# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**:- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ሚያዚያ 21 ቀን 2004 ዓ.ም.**

**የሙስሊሙ ህዝብ ከፍተኛ ተቃውሞ ሲያሰማ እንደነበር ተጠቆመ፤**

**የወያኔው መሪ አዲስ ምስጢራዊ ሰነድ ለስራ አስፈጻሚው ሰጠ፤**

**አርከበ እቁባይ ከንቲባ በነበረበት ወቅት 60 ሺህ ካሬ ሜትር መሬት የወሰደበት ሰነድ መገኘቱ ተጋለጠ፤**

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ መግለጫ በሰጠ በሶስተኛው ቀን በመላ ሀገሪቱ በሚገኙ መስጊዶች ከፍተኛ ተቃውሞ ሲስተጋቡ መዋላቸው ከተለያዩ ከተሞች የደረሰን ጥቆማ ገለጸ::

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ባሉ መስጊዶች እና በአወሊያ ትምህርት ቤት ውስጥ በተደረገው ተቃውሞ ለሰዓታት ያህል መንገዶች ሁሉ ተዘግተው እንደነበር ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ገልያ በተለይ በአንዋር መስጊድ የነበረው የፌዴራል ፖሊስ እና የሙስሊሙ ፍጥጫ በቀላሉ ሊበርድ የማይችል መስሎ እንደነበር በቦታው ተገኝቶ ዘግቦዋል::

በአንዋር መስጊድ ፤በቤኒን እና በአወሊያ ትምህርት ቤት ግቢና ውጭ በሚሊዮን የሚቆጠር የሙስሊሙ እምነት ተከታይ አዲስ አበባን በተቃውሞ ሲንጣት የዋለ ሲሆን ወያኔም ስጋት ስለገባው በየስርቻው የፌዴራል ፖሊሶችንና መትረየስ የጠመዱ መኪኖችን አሰማርቶ እንደነበረም ታይቶዋል::

ዓርብ ሚያዚያ 12 ቀን 2004 ዓ.ም በአንዋር እና በቤኒን መስጊዶች የሙስሊም እምነት ተከታይ የሆኑት በሙሉ ግልብጥ ብለው በመውጣታቸው የተነሳ መቆሚያ መቀመጫ ቦታ ጠፍቶ መንገዶች ሁሉ ተዘግተው ለብዙ ሰዓት መኪኖች በያሉበት ቆመው ለመቆየት እንደተገደዱ በስፍራው ተዘዋውሮ ከተመለከተው ዘጋቢያችን ለመረዳት ተችሎዋል::

EthioLion.Com

በፌዴራል ፖሊስ እና መትረየስ በጠመዱ ፓትሮል መኪኖች እያስፈራራ ተቃውሞውን ለመበተን ሙከራ ያደረገው የወያኔ ቡድን ሁኔታውን ሲመለከት እንደማያዋጣው በመረዳቱ በየስርቻው እየደበቀ እንደ ሰላይ በቅርብ ርቀት ሲከታተሉ እንደነበርም

ወጣት ፤አሮጊት፤ ሽማግሌ፤ህፃን ሳይል የሙስሊም እምነት ተከታይ ወደ መስጊድና ወደ አወሊያ መትመሙ ያስፈራው የወያኔ ቡድን በፌዴራል ፖሊስ ልዩ ከበባ ሲያደርግበት እንደነበር እና በፓትሮል ልዩ ጥበቃ ቢያደርግም ሙስለሙ ህብረተሰብ ድምጹን ከፍ አድርጎ ወያኔን ሲያወግዝና ሲያበጠለጥል መዋሉም ታውቆዋል::

ሙስሊሙ በ1966 ዓ.ም የኃይለስላሴን ስርዓት በቃወም ድመፁን ያሰማበት 38ኛ ዓመት ታስቦ እንዲውል በሚል በተመሳሳይ ዛሬም ሙስሊሙ በወያኔ ላይ ያለውን ጥላቻ በመላ ሀገሪቱ ባሉ መስጊዶች ተቃውሞውን ሲያስተጋባ እንደዋለ ከተለያዩ ከተሞች የደረሱን ጥቆማዎች ገልጸዋል::

የአወሊያ ትምህርት ቤት ከመንግስት ተፅዕኖ ነፃ ይውጣ......አሁን ያሉት የሙስሊሙ አመራሮች ከየት እንደመጡ አናውቅም ነጻ ምርጫ ተደርጎ ሙስሊሙ የመረጣቸው ይቀመጡ........አህባሽ የተባለ ወያኔ አመጣሽ ሀይማኖት የሙስሊሙን ህዝብ የሚበክል እና የተሳሳተ መንገድ የሚከተል በመሆኑ ከመላ ሀገሪትዋ ይጥፋ...... ሙስሊሙን ለመከፋፈል የሚደረገው ጥረት ይቁም ......የሚሉና ሌሎችንም ተቃውሞዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ሲያሰሙ የዋሉት ሙስሊሞች በተለይ መለስ በሰጠው መግለጫ እጅግ መከፋታቸውንም ማንሳታቸው ታውቆዋል::

ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው ሲከታተሉ የነበሩ ተቀማጭነታቸው አዲስ አበባ የሆኑ የብዙ ሀገራት ዲፕሎማቶችም በየመስጊዱ ሲካሄድ የቆየውን ተቃውሞ በካሜራ ሲቀርፁ እንደነበርና አንዳንድ የሙስሊም አባቶችንም ሲያነጋግሩ መታየታቸውን ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ገልፆዋል::

ህዝባዊ ተቃውሞው ለረጅም ሰዓት በመቀጠሉ የአስኮ፤የመርካቶ፤ እና የፒያሳ መንገዶች ተዘግተው ከመዋላቸውም በተጨማሪ ሌሎች የክርስትና እምነት ተከታዮችም አይዞዋችሁ ከጎናችሁ ነን ሲሉ ለመስሊሞቹ ድጋፍ ሲያደርጉ እንደነበርም ከተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

ተቃውሞው እየሰፋና እንቅስቃሴው እየጨመረ በመሄዱ ከፌዴራል ፖሊስ ጋር ግጭት እንዳይፈጠር በመስጋት የሙስሊም አባቶች ህዝቡን በመለመን እንዲበተን ያደረጉ ቢሆንም ወጣት እና ተቃውሞውን አንቀሳቃሽ ናቸው የተባሉትን ከ50 በላይ የሆኑትን ወጣቶች የደህንነት ሰዎች ዓርብ ዕለት ምሽት ከያሉበት ወስደው የት እንዳደረሱዋቸው እንደማይታወቅም ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል:: ታውቆዋል::

አላሁ አክበር!....... አላሁ አክበር!...... ለእምነታችን ስንል ለመሞት ተዘጋጅተናል .......እያሉ ወጣት...... አሮጊት .... ሽማግሌ ሳይል መላው የሙስለሊሙ እምነት ተከታዮች ተቃውሞዋቸውን በማስተጋባታቸው የተደናገጡት እነ መለስ ዜናዊ በማግስቱ ቅዳሜ አስቸኩዋይ ስብሰባ ስራ

EthioLion.Com

አስፈጻሚውን ጠርተው ሲመክሩ እንደነበር ከደረሰን መረጃ ለማወቅ ችለናል፡፡ በዚሁ ምስጢራዊ የስራ አስፈጻሚ አባሎች ስብሰባ ላይ በተነሳው አጀንዳ መሰረት ሙስሊሙ አሁን ባለው ሁኔታ ከቀጠለ የሰሜን አፍሪካ ሀገራት የፈጠረውን የፖለቲካ ቀውስ እኛም ላይ ሊፈጥር ስለሚችል አስደንጋጭ እርምጃ መውሰድ አለብን ሲሉም መወያየታቸው ታውቆዋል፡፡ ከኦህዴድ አራት የስራ አስፈጻሚ በጎደሉበት በዚህ የአስቸኳዋይ ስብሰባ ምስጢራዊ ውይይት ላይ በመለስ ዜናዊ የተዘጋጀ  አጭር ፅሁፍ የተሰራጨ ሲሆን ይህ ፅሁፍም ሙስሊሙ ለስርዓቱ ዋነኛ አደጋ እንደሆነ ጨምሮ ይዘረዝራል፡፡

ለስራ አስፈፃሚው ብቻ በምስጢር በተሰጠው በዚሁ ሰነድ ላይ «ከቅርብ ግዜ ወዲህ በሙስሊሙ ህዝብ ውስጥ መነጋገሪያ የሆነ አንድ ጉዳይ አለ፡፡የጉዳዩ አነጋጋሪነት ከጉዳዩ ባለቤቶች አልፎ ባለፉት ዓመታት የአዲስ ራዕይ (የወያኔ ወርሀዊ መፅሄት) እትሞቻችን ተከታታይ ፅሁፎች የዳሰስናቸው የከሰሩ ፖለቲከኞችን ትኩረትም ስቦዋል፡፡አንዳንዶቹም ዘወትር ውስጥ ውስጡን እያብሰለሰሉ አጋጣሚ ብቻ ለሚጠብቁለት የነውጥ አላማቸው አመቺ ሁኔታ እየተፈጠረ እንደሆነ ስለተሰማቸው ምክር..... ተግሳፅና ብይን ብጤ ለመስጠት ቢሞከርም በየጋዜጦቹ በሚያወጡዋቸው ፅሁፎች የውዥንብሩን አድማስ ይበልጥ ለማስፋት መታተር ጀምረዋል፡፡በጉዳዩ ዙሪያ በአመራሮች እና በአባላት ዘንድ ግልፅነት የለም »ሲል የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ለስራ አስፈጻሚው በበተነው ፅሁፍ ይዘረዝራል፡፡

ፅሁፉ አክሎም በኢትዮጵያ ውስጥ ተገኘ ስለተባለው የአልቃይዳ ሴል ከወሀቢያ ጋር በማወዳደር የዘረዘረ ሲሆን አንዳንድ ኃይሎች በሀገራችን የሚያራምዱዋቸውን ፀረ ህገ መንግስት የሆኑ አቋዋሞች ከህገ መንግስቱ ጋር አስተሳስሮ የመግለፅ ጉዳይ ሊኖር ይችላል ፡፡ማንም እንደሚያውቀው በእስልምና እምነት ስም የሚንቀሳቀስ ነገር ግን የእስልምና መሰረቶችን ከመናድ ጀምሮ ጸረ ህገ መንግስት አቋዋሞች የሚያራምድ ቡድን ኢትዮጵያ ውስጥ አለ"ሲልም ይገልጻል፡፡

በሙስሊሙ መሀከል ልዩነት ሊፈጥር በሚችል መልኩ ያሰፈረውን ሀሳብ ደግሞ እንዲህ ይላል " ከወርጂያዎች እና በወሀቢያ መሀከል ሰፊ ልዩነት አለ፡፡ወሀቢያ ከከወርጂያ በተለየ ሁኔታ በእውቀት እና በመማር ያምናል ፡፡ከዚህ ውጭ ባለው ፀረ ህገ መንግስት አቋዋሙ ከከወርጂያ አይለይም ፡፡ወሀቢያ በመሰረቱ መንግስትንና ሀይማኖትን ተነጣጥሎ መሄድ አይችልም የሚል አቋዋም የያዘ ቡድን ነው" ሲልም ያትታል፡፡

" ወሀቢያ በበቀለበት በሳዑዲአረቢያ እና ቀጥሎ  በተስፋፋበት ባህሬን ይህንኑ አቋዋም የሚያራመድ ነው፡፡ይኸው አቋዋሙ እንደኛ በመሰሉ የበርካታ የኃይማኖት ቤት በሆኑ ሀገሮች ቀርቶ ሙሉ በሙሉ ሙስሊም በሆኑትም የሺአዎችን እና የሱፊዎችን ህልውና በሀውየት በማጥፋት ጭምር በመፈታተን የሚታወቅ ነው፡፡ይህ አቋዋም ከእስልምና ጋር ምንም ዝምድና የለውም ፡፡ይልቁንም የእስልምና አስተምህሮዎችን ይፃረራል፡፡ይህ አቋዋም የፖለቲካ ይዘት ያለው አቋዋም ነው፡፡ይህን አቋዋም መተቸት እስልምናን መተቸት ሊሆን አይችልም" በማለት መለስ ዜናዊ በበተነው ፅሁፍ ላይ የዘረዘረ ሲሆን በተለይ በአሁኑ ወቅት የሙስሊሙ ንቅናቄ እጅግ ከባድ የሆነና ሌላውን የተቀረውን ህዝብ ጭምር የሚያንቀሳቅስ በመሆኑ አስቸኩዋይ እርምጃ በምስጢር መወሰድ አለበት ሲልም አብራርቶዋል፡፡

EthioLion.Com

ዛሬ በአዲስ አበባና በመላ ሀገሪትዋ የሙስለሙ ማህበረሰብ ያነሳው ተቃውሞ እየተቀጣጠለ ባለበት በዚህ ወቅት ችግሩን ለመቅረፍ ከሙስሊሙ አባቶች ጋር ለመወያየት በቤተ መንግስት ይዞት የነበረውን ፕሮግራም ሰርዞ ይህን አጭር ሰነድ አዘጋጅቶ ለስራ አስፈጻሚው መበተኑ እጅግ የሚያሳፍር ከመሆኑም በላይ እነ መለስ በምስጢር በሙስሊሙ ላይ አረመኔያዊ እርምጃ ለመውሰድ መዘጋጀታቸውን ያጋለጠ ነው ተብሎዋል::

ሙስሊሙ በአንድነት ከዳር እስከ ዳር በመላ ሀገሪቱ አቋዋሙን መግለፁ ያስደነገጣቸው እነ መለስ ዜናዊ በተለያዩ ሰበቦች ለመከፋፈል ጥረት ቢያደርጉም አልሳካ ስላላቸው ብቻ የአልቃይዳ ሴል ወደ ሀገር ውስጥ ገብቶዋል በሚል ሰበብ የንቅናቄው መሪ ናቸው የተባሉትን ለእስር እና ለእንግልት ሊዳርጉዋቸው መሆኑን ምንጮቹ አክለው ገልጸዋል::

ዓርብ ዕለት ሚያዚያ 12 ቀን 2004 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ውጭ ባሉ መስጊዶች ውስጥ ፖሊስ እና ሙስሊሙ ህዝብ ተጋጭተው ከፍተኛ ጉዳት የደረሰ ሲሆን በተለይ በሻሸመኔ፤በደሴ ፤በወልቂጤ ፤በጅማ ፤በባሌና አርሲ ብዙ ሙስሊሞች በፖሊስ መደብደባቸውን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አጋልጦዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ የወያኔው ስርዓት በኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴም ሆነ ከፍተኛ ባለስልጣናቱ ስላልተማመነ ከቅርብ ግዜ ወዲህ ኦህዴዶች በሞግዚት እንዲተዳደሩ መድረጉን የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ::

በህዝብ ብዛት እና በቆዳ ስፋቱ ትልቁ የሆነው የኦሮሚያ ክልልን የሚመራው ኦህዴድ ካድሬዎች ለስርዓቱ ዋነኛ አደጋዎች ናቸው በሚል በህወሀት ከፍተኛ ባለስልጣን በሆነ ግለሰብ የበላይነት እንዲመራ መደረጉ ተጋልጦዋል::

ከህወሀት ክፍፍል በፊት ኦህዴድንና የኦሮሚያን ክልል በበላይነት ሲመራ የነበረው ሰለሞን ጢሞ የተባለው የህወሀት ከፍተኛ ባለስልጣን የነበረ መሆኑን የጠቆሙት ውስጥ አዋቂ ምንጮች አባዱላ ገመዳ የክልሉ ፕሬዝዳንትና የኦህዴድ ሊቀመንበር ሆኖ ከተሾመ በሁዋላ የሚግዚት አስተዳደሩ ተነስቶላቸው የነበረ ቢሆንም ባለፈው ዓመት አባዱላ ተነስቶ አለማየሁ አቶምሳ የተባለው አዲስ ካድሬ ከተሾመ ወዲህ ግን አዲስ የበላይ ጠባቂ የህወሀት ከፍተኛ ባለስልጣን መቀመጡ ተጋልጦዋል::

ወያኔ ባወጣው ህገ መንግስት መሰረት ክልሎች እራሳቸውን በራሳቸው ያስተዳድራሉ ብሎ ያስፈረ ቢሆንም ከቅርብ ግዜ ወዲህ ግን የኦህዴድ ባለስልጣናት እና በተለይ ወጣት ካድሬዎች በሚያደርጉት እንቅስቃሴና በሚያነሱዋቸው አጀንዳዎች የተደናገጡት እነ መለስ ዜናዊ በጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ የክልሎች የበላጠይ ጠባቂ በሚል የህወሀት ከፍተኛ አመራር በሆነው ገብረ ተንሳይ ወ/ተንሳይ በተባለ ግለሰብ እንዲመራ መደረጉን ምንጮቹ አጋልጠዋል::

ህገ መንግስቱ ላይ በሰፈረው መሰረት ክልሉን የሚመራው በህዝቡ ከተመረጡ የህዝብ ተወካዮች መሀከል ይሆናል የሚል ቢሆንም ይህ ተግባራዊ ሳይደረግ በቅርቡ የተመረጠውን ፕሬዝዳንትም ሆነ ምክትል ፕሬዝዳንቶች ባለማመን ከትግራይ በመጣ ገ/ተንሳይ ወ/ተንሳይ በተባለ የህወሀት ሰው በስውር እንዲመራ መደረጉ በኦህዴዶች ዘንድ እያነጋገረ መሆኑንም ምንጮቹ አጋልጠዋል::

EthioLion.Com

የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ እንደሚያስረዳው ከሆነ በአሁኑ ግዜ የኦሮሚያን ክልል የሚመራው የክልሉ ሬዝዳንት አለማየሁ አቶምሳ ሳይሆን በጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ ውስጥ የሚገኘው የህወሀቱ ሰው ገ/ተንሳይ ወ/ተንሳይ የተባለው መሆኑን አጋልጠው በተለይ ከሁለት እና ሶስት ሳምንት ወዲህ እየታመሰ ባለው ኦህዴድ ውስጥ ይህ ጥያቄ ጎልቶ በመውጣቱ ለመለስና ለቡድኑ አደጋ እየተጋረጠበት መሆኑን አጋልጠዋል::

የስራ አስፈጻሚ የነበሩትን የኦህዴድ ከፍተኛ ባለስልጣናት ሲባረሩ ከፍተኛ ሴራ ሲሸርብ የነበረው ይሄው ግለሰብ እንደነበር የጠቆሙት ምንጮቹ ባጀቱም ሆነ ማንኛውም የክልልሉ እንቅስቃሴን በበላይነት እየመራ የሚገኘው ይሄው ገብረተንሳይ መሆኑን ምንጮቹ ጨምረው ገልጸዋል::

ከዚህ ቀደም ከህወሀት ክፍፍል በፊት የህወሀቶቹ ቁንጮ የነበሩት ሰለሞን ጢሞ የኦሮሚያን ክልል ሲመራ የነበረ ሲሆን ቢተው በላይ የተባለው ደግሞ የደቡብን ክልል በበላይነት ሲያሽከረክሩ እንደነበር ይታወሳል::

አሁን ደግሞ የኦህዴድ ወጣት የስራ አስፈጻሚና ማዕከላዊ ኮሚቴ አባሎች እንዲሁም የተማሩ የኦህዴድ ካድሬዎች ቅኝ መገዛት አንገሸገሸን እያሉ ተቃውሞ እያነሱ ህዝቡን እየቀሰቀሱ ነው በሚል ፍርሀት እርስ በርስ እንዲጠላለፉ ከመደረጋቸውም በተጨማሪ ሌላ ከትግራይ በመጣ ሰው በሞግዚት እንዲተዳደሩ መደረጉ አስገራሚና አስቂኝ ነው ሲሉም ምንጮቹ ይገልጻሉ::

በአሁኑ ሰዓት የክልሉ ፕሬዝዳንት እና የኦህዴድ ሊቀመንበር የሆነው አለማየሁ አቶምሳ ለካድሬዎቹ የሚሰጠው መመሪያና ትዕዛዝ ተግባራዊ ሳይደረግ በሚግዚት የሚመራው ገብተንሳይ ውሳኔ ግን ተግባራዊ እየተደረገ እንደሚገኝ ምንጮቹ አጋልጠዋል::

በቡድን መደራጀት.....አስተዳደራዊ በደል በመፈጸም......የመንግስትን መመሪያና ትእዛዝ አለመቀበል......በሚሉና በሌሎች ምክንያቶች ጠንካራ ናቸው የተባሉትን የኦህዴድ ካድሬዎች ለመመንጠር ብሎም ለመወንጀል ውስጥ ውስጡን ግምገማ በሚል አዲስ የጠለፋ ሴራ እየተውጠነጠነ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ የክልሉ ፕሬዝዳንት አለማየሁ አቶምሳ በማያውቀውና ባላመነበት ጉዳይ ላይ ሁሉ በግዴታ ፊርማ እንዲፈርም እየተደረገ በመሆኑ ቤቱ ውስጥ ለመዋል እንደተገደደ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ዘገባ ያስረዳል::

በመጨረሻም በአንድ ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ሆኖ ሲሰራ የነበረው አርከበ እቁባይ 60 ሺህ ካሬ ሜትር  መሬት በአዲስ አበባ ውስጥ በተለያዩ ቤተሰቦቹ ስም የወሰደበት ሰነድ መገኘቱን ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ አጋለጡ:: የቀድሞው ከንቲባ አርከበ እቁባይ በቤተሰቦቹ ስም መሬት እየሸነሸነ ለግሉ ያግበሰበሳቸው 60 ሺህ ካሬ ሜትር መሬት መውሰዱን የሚያረጋግጥ ሰነድ መገኘቱ የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ::

EthioLion.com